# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 299 ጥር 23 2006 ገጽ 1

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ህወሃቶች ስሙ! እናንተ ጭካኞች ናችሁ። ይሄን ጭካኔያችሁን ጀግንነት ብላችሁ ትጠሩታላችሁ። ጀግናና ጨካኝ ግን ለየቅል ናቸው። ጀግና ሌባ አይደለም። ጀግና ዛሬ የተናገረውን ነገ አይክደውም። ጀግና ወገኑን በሃሰት ከሶ በሃሰት አስመስክሮ የሞት ፍርድ አያስፈርድም። ጀግና ክፉን ከደጉ ያለየን ህፃን በጥይት ደብድቦ ለመግደል ርህርሄ የጎደለው አይደለም። ጀግና እኔ ብቻ የሚል ስግብግብ አይደለም። ጀግና በአባቶች ደምና አጥንት የቆየን አጥር ቅጥር አፍርሶ የባእዳን መጫዋቻ አያደርግም። ጀግና አገርን ድርና ማግ ሁነው የሚያቆሙ እሴቶችን እየበጣጠሰ ጥሎ የአገርን መሠረት ሲያፈርስ አይገኝም።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የአሜሪካ ኮንግሬስ ኢትዮጵያ ዉስጥ ዜጎቿን ማፈናቀል ካላቆመች የኦባማ አስተዳደር የሚሰጠዉን ዕርዳታ እንዲያጤን ጠየቁ

ታሪካዊና በወያኔ አገዛዝ ለሚማቅቁ አያሌ ኢትዮጵያውያን እያደረጉት ላለው ትግል ስኬትን የሚፈነጥቅ የተባለለት ውሳኔ አሜሪካን ጨምሮ ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ድጋፍ የሚያደርጉ አለማቀፍ የገንዘብ ተቋማት፣ ለኢትዮጵያ የሚሰጡት ማንኛውም ድጋፍ ዜጎችን የማያፈናቅል እና ሰብአዊ መብቶችን የማይጥስ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው ሲል በአፅንኦት ያሳስባል። ይህ ውሳኔ የጉጅሌው ወያኔ እኩይ ስራ በአለማቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ እየታወቀ እንደመጣ አመላካች ነውም ተብሏል። ፋሽስቱ ወያኔ በሃገሪቱ በአራቱም ማዕዘናት የሚኖሩ ዜጎችን በስፋት በማፈናቀል በልማት ስም መሬታቸውን ለውጭ ባለሃብቶች በመቸብቸብ፡ በሽርክነትም በመስራት የአገዛዙን ካዝናና የአገልጋይ ካድሬዎችን ኪስ በማድለብ ዜጐችን ለከፋ ችግር ከመዳረጉም በላይ ዜጐች በሃገራቸው የባዕድነት ስሜት እንዲሰማቸው እያደረገ የሚገኝ የባንዳ አገዛዝ መሆኑ ይታወቃል። በፋሽስቱ ወያኔ የማፈናቀል የጥፋት በትር ካረፈባቸው አካባቢዎች መካከል የአሞ ሸለቆና ጋምቤላን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## መከረኛዋ ቁጫ አሁንም መከራዋን እያየች ነዉ - ነዋሪዎቿ አሁንም እየተገደና እየታሰሩና ነዉ!

ፋሽስቱ ወያኔ በቁጫ ወረዳ እያደረሰ ያለውን ሽብር እንዲያቆም ሰመጉ (የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ) ጠየቀ፡ ግድያው እስርና ድብደባው በመቀጠሉ ነዋሪው በፍራቻ አካባቢውን በመሸሽ ወደ አጐራባች ከተሞች ነፍስ አውጭኝ ሽሽት ላይ እንደሆኑም ድርጅቱ አጋልጧል። በቁጫ የማንነት፣ የመልካም አስተዳደርና የልማት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የተነሳውን የህዝብ ብሶትና ተቃውሞ አሁንም ድረስ ማብረድ ያልተቻለ ሲሆን፣ ፋሽስቱ ወያኔም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጸረ ሰላም ሃይሎች እጅ አለበት በሚል ስጋት በአካባቢው ነፍሰ ገዳይ ቅጥረኛ የጸጥታ ሃይሎች እንዳሰማራ ለማወቅ ተችሏል። ሰመጉ በአደባባይ በርካታ ሰዎች መገደላቸውን፡ ከ400 በላይ ሰዎች ታስረው ከፍተኛ ድብደባ እየተፈፀመባቸው መሆኑን፡ ከሚደርሰው መንገላታት እና ጥቃት ለማምለጥ በሺህዎች የሚቆጠሩ የወረዳው ነዋሪዎች ወደ አጎራባች አካባቢዎች እየተሰደዱ መሆናቸውም ታውቋል ብሏል በመግለጫው። በርካቶችም ከስራ ገበታቸው መባረራቸውን በማከል፡ አገዛዙ በንፁሃን ዜጐች ላይ እየፈፀማቸው ካላው አሰቃቂ ወንጀሎች ማለትም ከግድያ፣ ከአካል ማጉደል፣ ድብደባ፣ ሕገ-ወጥ የቤት ብርብራ፣ ህገ-ወጥ እስርና፣ ከስራ ማሰናበት እንዲታቀብ፡ በየአጎራባች አካባቢዎች ነፋሳቸውን ለማትረፍ የተሰደዱትም ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው እንዲመለሱ በአፅንኦት ጠይቋል።

## ወያኔ ለሱዳን አሳልፎ የሚሰጠው የአገራችን መሬት ጉዳይ ኢትዮጵያዉያንን በያሉበት እያስቆጣ ነዉ

አጼ ቴወድሮስንና አጼ ዮሐንስን ጨምሮ ብዙ የሀገራችን ነገስታትና የአካባቢው አስተዳዳሪዎች የተዋደቁበት፣ እልፍ አእላፍ ወገኖቻችን ደማቸውን ያፈሰሱለትና አጥንታቸውን የከሰከሱለት ከሱዳን ጋር በምንዋሰንበት በኩል ያለውን እጅግ ረጅም የሀገራችንን ድንበር ፋሽስት ወያኔ ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት እጫፍ እንደደረሰ በመሰማቱ በዓለም ዙሪያ ከፍተኛ ተቃውሞ ማስነሳቱ ታወቀ።

ይህን የፋሽስት ወያኔ ድርጊት ለመቃወም በሀገር ውስጥ ሰማያዊ ፓርቲ የተቃውሞ ሰልፍ የጠራ ቢሆንም ከወዲሁ ከፍተኛ መሰናከል እየገጠመው መሆኑ ተሰምቷል። ፌስ ቡክንና ፓልቶክ ክፍሎችን በመሳሰሉት የማሕበራዊ መገናኛ መድረኮች ላይ የሚሰማውና የሚታየው ተቃአውሞ ግን እድሜና ጾታ፣ የተማረ ካልተማረ፣ ፋሽስት ወያኔን ከሚደግፉት እስከሚቃወሙትና ሃየማኖትንም ሳይለይ ሀገርን መአከል አድርጎ የተደረገ እንደነበር ዘገቢያችን የታዘበውን ገልጿል።

ከዚህ በፊት የህንኑ የሀገራችንን ድንበር አስመልክቶ ምሁራንና የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች በተለያየ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ ተቃውሞ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ሰሞኑን የተለቀቀው የዘንድሮው የሂውማን ራይትስ ወች ሪፖርት የወያኔን አፈና በድጋሚ አጋለጠ

ወያኔ በሆድ አደር በለስልጣናቱ አማካኝነት እስኪሰለቸን በመደጋገም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ራእይ የለሽነትና ደካማነት እንጅ ሀገሪቱ ለፖለቲካ ጨዋታ ምቹ ናት፤ የሀገራችንን ብርቅ ነጻ ጋዜጠኞች ራሱ ሽብርተኛ እያለ ለሚጠራቸው ፖለቲካ ድርጅቶች ይወግናሉ፤ ወይም ደግሞ የሽብርተኛ ድርጅቶች ጉዳይ አስፈጻሚዎች ናቸውና የመሳሰሉትን እየደረደረ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲዋሽና ዓለምን ሲያታልል ቢከርምም እንሆ ዓለማቀፍ እውቅና ባላቸው ድርጅቶች ሪፖርት በተደጋጋሚ እየተጋለጠ መሆኑ እየታየ ነው።

ሰሞኑን የወጣው የ2013ን እንቅስቃሴ የሚገመግመው የሂውማን ራይትስ ወች ሪፖርት እንደሚያመለክተው ግን ፋሽስት ወያኔ ለራሱ ህልውና ይጠቅመው ዘንድ የፖለቲካ ምህዳሩን በማትበብ ማንም ግለሰብም ሆነ ፖለቲካ ፓርቲ ሊነቀሳቀስ ከማይችልበት ደረጃ ላይ እንዳደረሰው አጋልጧል። ይህ የድርጅቱ ሪፖርት የነጻ ሚዲያ ህልውና በኢትዮጵያ ከፍተኛ አደጋ ውስጥ እንደወደቀ ጨምሮ አጋልጧል።

ከጥቂት አመታት በፊት ፋሽስት ወያኔ ባጸደቀው የጸረ ሽብርተኝነት አዋጅ የተነሳ ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች ሽብርተኛ ተብለው እንደታሠሩና እንደተፈረደባቸው የጠቀሰው የተቋሙ ሪፖርት በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በፍርሃት ቆፈን ውስጥ እንዲቀመጡ ተደርገዋል ብሏል። ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችም ከልክ በላይ እየተባባሱ መምጣታቸውን የጠቀሰው ሪፖርት ህጋዊ ታራሚዎች በተለይም ጋዜተኞችና ፖለቲካ እስረኞች በገለልተና አካላት እንዲይጎበኙ እገዳ ይታልባቸዋል ሲል አጋልጧል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ/ኢህአዴግ የልማት ዕቅዴን ተግባራዊ ለማድረግ 50 አመት ያስፈልገኛል አለ

ጠ/ሚንስትር ሃይለማርያም ደሳለኝን በአማካሪነት ከከበቡት አንድ ደርዘን ሰዎች ዉስጥ አንዱ የሆነዉ መርዘኛዉ በረከት ስምኦን ሰሞኑን ለገዢዉ ፓርቲ ከፍተኛ ካድሬዎች ባደረገዉ ንግግር ኢህአዴግ የልማት ዕቅድ ብሎ የያዛቸዉን ስራዎች ተግባራዊ ለማድረግ ከ40 አሰከ 45 አመታት እንደሚያስፈልጉት ተናገረ። በረከት ስምኦን በዚህ ከፓርቲዉ አባላት ዉጭ ለማንም ሰዉና ድርጅት ዝግ በሆነ ስብሰባ ላይ ባቀረበዉ ጥናታዊ ጽሁፍ ኢህአዴግ የህዝቡን የነፍስ ወከፍ ገቢ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለማድረስ ቢያንስ ከ40 እስከ 50 ዓመታት እንደሚያስፈልገው ገልጸዋል። በረከት ስምኦን በዚሁ “የወደፊቱ የህዳሴ መንገድ” በሚል አርዕስት በቀረበዉ ጥናታዊ ዘገባ ላይ፣ ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ህዳሴ በስንት ዓመታት ሊጠቃለል ይችላል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ከእነኮሪያና ታይዋን ልምድ መቅሰሙን ተናግሯል። እንደ በረከት ስምኦን አባባል ኮሪያና ታይዋንን የመሳሰሉ አገሮች ከዝቅተኛ ወደ መካከለኛ ከዚያም ወደ ከፍተኛ ገቢ ለመድረስ ከ40 እስከ 50 ዓመታት ስለወሰደባቸዉ ኢትዮጵያም በዚህ ስሌት በሃምሳ አመታት የህዳሴ ጉዞዋን ትጨርሳለች ብሏል። የበረከት ስሌት የሚያመጣዉን ዉጤት የማይመኝ ኢትዮጵያዊ የለም፤ ሆኖም በረከት ስሌቱን ሲሰራ የወያኔ/ኢህአዴግ ለኢትዮጵያ ጥቅም ግድ የሌለዉና ሊወድቅ አንድ ሀሙስ የቀረዉ ዘረኛ ስርዐት መሆኑን የስሌቱ ግብዐት አድርጎ አልወሰደዉም።

( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## አንድ አለማቀፍ ተቋም ወያኔ የግንቦት 7 መሪዎችን በዉድ ዋጋ በተገዛ የስለላ መሳሪያ እንደሚሰልል ደርሼበታለሁ አለ

የዜጎችን ደህንነት ከመንግስታት ጥቃት ለመከላከል የተቋቋመው ፕራይቬሲ ኢንተርናሽናል የተባለው ተቋም ለእንግሊዝ መንግስት የገቢዎቸና ጉምሩክ መስሪያ ቤት በጻፈው ደብዳቤ “ጋማ ኢንተርናሽናል የተባለው የእንግሊዝ ኩባንያ በአለም ላይ የሰብአዊ መብቶችን በመጣስ ለሚታወቁ አገሮች ኮምፒይተሮችን፣ የሞባይልና የስካይፐ የስልክ ግንኙነቶችን እንዲሁም የኢሜል ልውውጦችን በርቀት ሆኖ ለመከታተል የሚያስችለውን ፊን ፊሽር ወይም ፊን ስፓይ በሚል ስም የሚጠራውን የመሰለያ መሳሪያ ከአውሮፓ ህብረት ውጭ ላሉ አገሮች በመሸጥ ዜጎች እንዲሰለሉና ደህንነታቸው አደጋ ላይ እንዲወድቅ በማድረጉ ምርመራ እንዲጀመር” ሲል ጠይቋል።

የግንቦት7 ከፍተኛ አመራር በሆኑት በ ዶ/ር ታደሰ ብሩ የግል ኮምፒዩተር ላይ የመሰለያ ቫይረሱ መገኘቱን በቶሮንቶ ዩኒቨርስቲ የሙንክ ስኩል ግሎባል ጉዳዮች የምርምር ተቋም የሆነው ሲትዝን ላብ ማረጋገጡን ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የግንቦት ሰባት መንገድ

ህወሃት-ኢሕአዴግ አዲስ ቀረርቶ ጀምሯል። የግንቦት ሰባት መንገድ የሚል። የግንቦት ሰባት መንገድ ምንድ ነች ለሚለው በተደጋጋሚ ለህዝባችን የነገርን ቢሆንም ቢነገራቸው ለማይሰሙት፤ ቢሰሙትም ማስተዋል ለማይችሉት ለህወሃታዊያን እንደገና ልናስታውሳቸው ፈቅደናል እንነግራችዋለን ።

ህወሃት-ኢሕአዴጎች ማድመጥ ትችሉ እንደሆነ አድምጡ። መንገዳችን አዳናጋሪ አይደለችም። መንገዳችን እናንተ ያሰራችሁትን ማስፈታት፤ እናንተ "እኛ ከሌለን አገሪቷን እናፈርሳታለን ብላችሁ የምትቃገፉትን ቅዠት" በቅዥትነቱ እንዲቀር ማድረግ፤ `በህዝባችን ላይ የመዘዛችሁትን የጥፋትሰይፍ ወደ ሰገባው እንድትመልሱ፤ ዝሪፊያችሁንና ቀማኛነታችሁን ትታችሁ እንደ ጤነኛ ሰው ማሰብ እንድትችሉ፤ ከህዝብ ዓይንና ጆሮ ሰውራችሁ የምትፈፅሙትን ወንጀል እንድታቆሙ የምታደርግ ነች። ይህች መንገድ እንደምን ሆና አደናጋሪ ትሆናለች?

ዛሬ ኢትዮጵያዊያንን ነፃነታቸውን በሙሉ ገፋችሁ ስታበቁ *"ተኛ ብንለው ይተኛል፤ ተነስ ብንለው ይነሳል፤ ብንበድለውም ይሸከመናል"* እያላችሁ እንደምትሳለቁበት እናውቃለን። እንግዲህ የእናንተ መንገድ ይሄው ነው። ህዝቡን አገር አልባ አድርጋችሁ፤ መብቱን በሙሉ ገፋችሁ ፍፁም ተገዢያችሁ ማድረግ። አዎን አገሩን የተነጠቀ ሰው በረከት ስምዖን እንደሚለው ተኛ ሲባል የሚተኛ፤ ተነስ ሲባል የሚነሳ፤ ሲበደልም በደሉን ተሸክሞ በፍፁም ፍርሃት ውስጥ ሆኖ የሚኖር ይሆናል። የህወሃት-ኢሕአዴግ መንገድ መጨረሻው ዜጎች በፍፁም ፍርሃት ተተብትበው ተገዢ ሆነው እንዲኖሩ ማድረግ ነው። ህውሃታዊያን ይሄን ትልቅ ውድቀት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ስኬታችን ነው ብለው በየስብሰባቸው መካከል መወያያ ሲያደርጉት አለማፈራቸው በእጅጉ የሚገርም ነው። ህወሃታዊያን ሆይ ስሙን ! የእኛ መንገድ ዜጎች የአገራቸው ባለቤት እንዲሆኑ የምትጠይቅ ነች። የአገሩ ባለቤት የሆነን ዜጋ በረከት ስምዖንን የመሰለ ማንነቱን የካደ ደካማ ካድሬ ተኛ ተነስ እያለ ሊያዋክበው አይደፍረውም። የአገሩ ባለቤት የሆነን ዜጋ ከአንዲት መንደር ተለቃቅመው የተደራጁ ዘራፊዎች በደል ሊፈፅሙበት በፍፁም አይችሉም። የአገሩ ባለቤት የሆነም ዜጋ እንዲህ አይነቶቹን በምንም መንገድ አይታገሳቸውም። የእኛ መንገድ ይህች አገር የእኔ ነች፤ አንተ ተኛ ተነስ እያልክ የምታዋክበኝ ማነህ ብሎ ለመጠየቅ አቅሙ ያለው ዜጋ እንዲፈጠር የምታደርግ ነች። በዚህች መንገድ ጭካኔን ከጀግንነት ለይተው የሚያውቁ ብዙ ኢትዮጵያን ጉዞ ጀምረዋል።

ህወሃት-ኢሕአዴግ እያላችሁ ራሳችሁን የምትጠሩ ሆይ ስሙ !

"እኛ ከሌለን አገሪቷን እናፈርሳታለን" እያላችሁ እንደምትፎክሩም እናውቃለን። ይህች አባባላችሁ ለአገር፤ለወገን እና ለትውልድ ምንም ዓይነት በጎ ምኞት እንደሌላችሁ የምትመሰክር መሆኗን መርሳት የለባችሁም። ለአገሩ በጎ ምኞት ያለው ቡድን "እኛ ካቃተን ሌላው ይሞክረው" ብሎ መድረኩን ለሌላ እችላለሁ ለሚል ይለቃል እንጂ "እኔ ከሌለው" ብሎ ጥፋት አይመኝም። እኛ ግን እንዲህ እንላችኋለን እውነት እውነት እንላችኋለን ዓይናችሁ እያየ፤ጆሮአችሁም እየሰማ እናንተ መፍረስና መበታተን የምትመኙላትን አገር ያለ እናንተ መልስን እንገነባታለን። የግንቦት ሰባት መንገድ እናንተ እናፈርሳታለን እያላችሁ የምትዝቱባትን አገር እንደማትፈርስ፤ ህዝቧም እንደማይበተን የምታደርግ ነች። ይህችን መንገድ ዘግታችሁ እንደማትዘልቁ ልታውቁ ይገባችኋል።

እናንተ ህዝባችንን ከአገሩ ጉዳይ አግልላችሁ በስውር ብዙ ወንጀሎችን እንደምትፈፅሙም እናውቃለን። ከሃውዜን እስከ ጃን ሜዳ የተቀበረው ወንጀላችሁ ከህዝብ ዓይን ተሰውሮ የሚቀር አይመሰላችሁ። ሚሊየኖችን ለችጋር አጋልጣችሁ ሚሊየነሮች እንደሆናችሁም የታወቀ ነው።አለቃችሁ መለስ ዜናዊ 3 ቢሊዮን ዶላር ሰርቆ በውጪ አገር ባንክ ውስጥ መደበቁን ዓለም ያወቀው እውነት ነው። እናንተም ጭፍሮቹ በድሃ ራስ ላይ ሚሊየነሮች ለመሆን መብቃታችሁም እውነት ነው። የግንቦት ሰባት መንገድ ይህ ዝርፊያችሁን በአደባባይ እንዲነገር የምታስችል ነች። ይህ እንዲሆን ደግሞ ነፃ ህዝብ፤ ከህግ በታች የሆነ መንግስታዊ ተቋም እና አንዱ አንዱን ያልተጫኔነበት፤ ሌላውም ሌላውን ያልተሸከመበትን ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ የመንገዳችን መዳረሻ ነው።

ህወሃት-ኢሕአዴጎች ስሙ! እናንተ የተወለዳችሁበትን የበቀለኝነት ስሜት ልተው አልቻላችሁም። የበቀል ሰይፋችሁ ይበልጥ እየሰላ ሄደ እንጂ አልረገበም። በቀለኝነታችሁንም እንደ ትልቅ ጀግንነት ትቆጥሩታላችሁ። እግራችሁ በረገጠበት መንደር በዜጎች መካከል ጥላቻ ተፈጥሮ ደም መፋሰስ ይሆናል እንጂ ሠላም አይሆንም። ህወሃቶች "አማራ እንደ ድርቅ የትግራይ ህዝብ ቀንደኛ ጠላት ነው" ብላችሁ የምታምኑ ቡድኖች ናችሁ። ይሄን እምነታችሁን በተግባር ለመፈፀም ተግታችሁ የሠራችሁ ቡድኖች ስለመሆናችሁም ከበቂ በላይ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። ለአብነት ያክል በዚሁ በእናንተ ዘመነ መንግስት ከ2ሚሊዮን በላይ አማራ የገባበት ሳይታወቅ መቅረቱን ማቅረብ ይቻላል። ይሄ ሁሉ አማራ የት እንደገባ መልስ ለመስጠት የደፈረ መንግስታዊ አካል እስከ አሁን አልተገኘም። አማራን እወክላለሁ የሚለው ድርጅት መሪዎች እነ አዲሱ ለገሠ፤ ተፈራ ዋልዋ፤ ህላዌ ዮሴፍ፤በረከት ስምዖንና ሌሎች ጀሌዎቻቸው ይሄን ጉዳይ በዝምታ ማለፋቸው አገሩን ያስደመመ አቢይ ጉዳይ ሆኖ ይቆያል። የሚያሳዝነውና የሚገርመው ሁሉ በደጃችሁ፤ ሁሉ በእጃችሁ ሆኖ ሲበቃም የበቀል ሰይፋችሁ ወደ ሰገባው አለመመለሱ ነው።ይህን የእናንተን የበቀለኝነት ስሜት ማብረድ አንዱ የግንቦት ሰባት መንገድ መሆኑን እወቁት።የግንቦት ሰባት መንገድ አንዱን ህዝብ የአንዱ ጠላት አድርጎ ርካሽ የፖለቲካ ጥቅም ለማግኘት መኳተን አይደለም። የግንቦት ሰባት መንገድ እናንተ ሃውዜን ላይ እንዳደረጋችሁት ህዝብን አስጨርሾ የደም እንጀራ መብላት አይደለም። የግንቦት ሰባት መንገድ ዜጎች ሁሉ በእኩልነት እና በነፃነት ኢትዮጵያ የእኔም አገር ነች ብለው በሠላም እንዲኖሩ እንጂ እርስ በርሳቸው እንዲጠላሉና ግጭት ውስጥ እንዲገቡ አይደለም።

ህወሃቶች ስሙ! እናንተ ጭካኞች ናችሁ። ይሄን ጭካኔያችሁን ጀግንነት ብላችሁ ትጠሩታላችሁ። ጀግናና ጨካኝ ግን ለየቅል ናቸው። ጀግና ሌባ አይደለም። ጀግና ዛሬ የተናገረውን ነገ አይክደውም። ጀግና ወገኑን በሃሰት ከሶ በሃስት አስመስክሮ የሞት ፍርድ አያስፈርድም። ጀግና ክፉን ከደጉ ያለየን ህፃን በጥይት ደብድቦ ለመግደል ርህርሄ የጎደለው አይደለም። ጀግና እኔ ብቻ የሚል ስግብግብ አይደለም። ጀግና በአባቶች ደምና አጥንት የቆየን አጥር ቅጥር አፍርሶ የባእዳን መጫዌቻ አያደርግም። ጀግና አገርን ድርና ማግ ሁነው የሚያቆሙ እሴቶችን እየበጣጠሰ ጥሎ የአገርን መሠረት ሲያፈርስ አይገኝም። እንግዲህ ህወሃቶች ያልፈፀማችሁት እኩይ ነገር ምንድ ነው? እናንተ አንዳችም የጀግንነት ጠባይ የሚታይባችሁ አይደላችሁም።ጠባያችሁ የፈሪና የጨካኝ እንጂ የጀግና አይደለም። የግንቦት ሰባት መንገድ እንዲህ ዓይነት ጨካኞችን ከህዝብ ጫንቃ ላይ አውርዳ ጥላ ህዝቡ የአገሩ ባለቤት እንዲሆን ማድረግ ነው።

ህወሃት-ኢሕአዴጎች ሆይ ስሙ ! ወደ ስልጣን ከመጣችሁ ግዜ ጀምሮ በወይኒ ጨምራችሁ የምታሰቃዩዋቸውን ዜጎች ታውቃላችሁ። በህግ ጥላ ሥራ ናቸው ብላችሁ ስታበቁ ትውልድ እንዳይተኩ ብልቶቻቸውን እንደምትቀጠቅጡ እኛ እናውቃለን።የተወልዱበትን ብሄር በጠቅላላው እንደምትሳደቡና እንደምታወረዱም ጭምር እናውቃለን። እንዲህ ያገኛችሁትን ሁሉ እንዳሰራችሁ እና እንዳሰቃያችሁ አትቀጥሉም። እናንተ ከህግ በላይ ሁናችሁ በሠራችሁት ህግ ዜጎችን እያሳደዳችሁና እያሰቃያችሁ እስከ መጨረሻው አትቀጥሉም። የእኛ መንገድ እንዲህ ያለውን ግፉ የምታስቆም ነች። የእኛ መንገድ መንግስት ህዝብን ፈርቶ እንጂ ህዝብን አስፈራርቶ ሲፈልግ ተኙ፤ ሳይፈልግ ደግሞ ተነሱ እያለ ህዝቡን ተጭኖ እንዳይኖር የምታደርግ ነች።መንገዳችን ለፍትህ፤ ለፃነትና ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ግንባታ የምትፋጠን እንጂ በነፃነት የምትሳለቅ፤ በፍትህ የምትቀልድ እና በዴሞክራሲያዊ እሴቶች ላይ የምታላግጥ አይደለችም።

በመጨረሻም በመንገዳችን ብዙዎች ጉዞ ጀምረዋል።ጉዞአችን የሚጠይቀውን ማንኛውንም መስዋዕትነት ለመክፈል የቆረጡ ጀግኖች ተነስተዋል።ፍትህን፤ ነፃነትንና የዴሞክራሲ እሴቶችን ፍለጋ የተነሳን ዜጋ ትዕቢት፤ ውሸትና ጭካኔ አይገቱትም። ህውሃት-ኢሕአዴጎች ስሙ እኛ ተነስተናል።ትግላችንም ጥሩ መሠረት ይዟል። ካሁን በኋላ በአገራችን ኢትዮጵያ ፍትህ ነግሶ፤ የነፃነት ጎህ ቀዶ፤ዴሞክራሲ አብቦ ሳናይ አንመለስም። ስለዚህ የህወሃት-ኢሕአዴጎች ጭካኔ የመረራችሁ፤ ውሸታቸው የሰለቻችሁ፤ ትእቢታቸው የታከታችሁ፤ በእነዚህ ቡድን የሚፈፀመው ወንጀል ጆሮአችሁን ጭው ያደረጋችሁ ሁሉ ኑና የጀመርነውን ትግል ተቀላቀሉን። እኛ ሳናፈገፍግ ልንታገል ተነስተናልና ኑና በግንቦት ሰባት በፍትህ፤ በነፃነትና በዴሞክራሲ መንገድ እስከ መዳረሻው ድረስ አብረን እንገስግስ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## የአሜሪካ ኮንግሬስ ኢትዮጵያ ዉስጥ ዜጎቿን ማፈናቀል ካላቆመች . . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ወሳኔውን አስመልክቶ የኦክላንድ ተቋም ዋና ዳይሬክተር የሆኑት አኑራዳሃ ሚታል፡ ውሳኔው የአሜሪካ እርዳታ እስከ ዛሬ ሲሰጥበት የነበረውን የተሳሳተ መንገድ ያስተካክላል ካሉ በኋላ፡ ከእንግዲህ የሰብአዊ መብቶችን እንዳሻቸው እየጣሱ በልማት ስም እርዳታ በማወናበድ መውሰድ እንደማይቻል ለማፍያው የወያኔ ቡድን ግልጽ መልእክት ያስተላለፈ ታሪካዊ ውሳኔ ሲልም አሞካሽስቶታል። ወያኔ በልማት ስም ከአለም አቀፍ መንግስታት በአመት ብዙ ሚሊዮን ዶላሮችን በማጭበርበር ሲያጋብስ እንደነበረ፡ የወያኔ ቱባ ካድሬዎችም የሚመጣውን እርዳታ ያለምንም ከልካይ እየመዘበሩ በውጫ ባንኮች አከማችተው ለግል ጥቅማቸው እያዋሉት እንደሚገኝ በተደጋጋሚ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃኖች መዘግቡ ይታወሳል።

---

# የወያኔ ነፍስ በበረከት ስምዖን በኩል ስትቃዥ

( በነፃነት ዘለቀ - ክፍል 2 የመጨረሻ ክፍል )

የኢትዮጵያን ገበሬ ኑሮ በረከት አያውቀውም ማለት ዘበት ነው፡፡ የኢትዮጵያን ገበሬ ወያኔ አያውቀውም ብሎ በዚህ ሰውዬ ንግግር መደመምም ከንቱ ነው፡፡ በገበሬው መቀለድ አምሯቸው እንጂ የሚናገሩት ነገር እውነቱ የተገላቢጦሽ መሆኑን አጥተውት አይደለም፡፡

ስለሆነም በረከት የሚለው ነገር "አይሰማም!" እንላቸዋለን ፡፡ በረከት ልፋ ብሎት ተናገረ የተባለውን ይናገር እንጂ የራሱ ስብሰባ አባላት ሳይቀሩ ሲችሉ በግልጥ ሳይችሉ ደግሞ በውስጣቸው ይስቁበታል፡፡ ለዚያውም ከትከት ብለው ነው እሚስቁበት - እንደጅል በመቁጠር፡፡ እርግጥ ነው - በረከት ጅል አይደለም፡፡ ጅል ለመምሰል የቆረጠው ግን ምርጫ በማጣት ይመስለኛል፡፡ አንድ ሰው ፀሐይ የሞቀውን እውነት ለመሸፈን በመሞከር በግልባጩ ለማውራት ከተገደደ አንድም ያስጨነቀው ነገር አለ ማለት ነው፤ አለበለዚያም የመዋሸት ተፈጥሯዊ ጠባይ አለበት ማለት ነው - ልክ እንደመለስ ዜናዊ፡፡ መለስ ዜናዊ በሣይንስ የተረጋገጠ ላይሆን ይችላል እንጂ በእንግሊዝኛው 'pathological liar' የሚባል ዓይነት ግለሰብ እንደነበር መረዳት አይቸግርም፡፡ እርሱ በቲቪ ቀርቦ የሚናገራቸውን ንግግሮችና መሬት ላይ ይታይ የነበረውን እውነት በማስተያየት የዚህን ሰው ውሸት በመናገር የመርካት ጠባይ ወይም የተዛባ ተፈጥሯዊ ባሕርይ በቀላሉ መገንዘብ ይቻል ነበር፡፡ በዚህ መልክ ይህ ተጋቦታዊ ደዌ በትግል አጋርነትና በጥቅም ተጋሪነት ምክንያት ለበረከትም ተርፎ ይሄውና በረከትም አንድም ሰው ላያምነው - አንድም የራሱ ሰው ሳይቀር አምኖ ላይቀበለው - እንዲሁ ድከም ብሎት ሲወሻክት እናደምጠዋለን፡፡ እስከመቼ እየወሻከተ በሰው ስቃይ ሲደሰትና የሰውን ስቃይ ለሚዲያ ፍጆታ ያህል ለከንቱዎች በመሸጥ እንደሚኖር ገና የምናየው ይሆናል፡፡ ወደኋሊናው የሚመለስ አይመስለኝም እንጂ ከተመለሰ ግን የገበሬውም ሆነ የአጠቃላዩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ካሉት በታች ከሞቱት በላይ የሆነ የሰቆቃ ሕይወት በሚያሳድርበት የእርግማን መዘዝ እንደይሁዳ ራሱን ሰቅሎ እንደሚገድል አምናለሁ፡፡ ያ ቀን ደግሞ በጣም ቀርቧል፤ ምን አለ በሉኝ እነዚህ ጉዶች የሥራቸውን የሚከፈሉበት ጊዜ በብርሃን ፍጥነት እየገሰገሰ በመምጣት ላይ መሆኑ ይሰማኛል፡፡ ቋቱ ሞልቷል፤ የሚቀረው የሚጠራርጋቸውን ማዕበል የሚያስነሣው የፈጣሪ ፊሽካ ብቻ ነው፡፡

የኃጢአት ትንሽና ትልቅ ባይኖረውም አንድ ሰው ሰርቆ ቢበላ እርቦት ሊሆን ይችላልና ምንም አይደለም ሊባል ይችላል፤ ቢሳደብ ተናድዶ ሊሆን ይችላል በሚል ይቅርታ ሊደረግለት ቢችል ምንም አይደለም፡፡ ነገር ግን በመንግሥት ሠራሽ ርሀብና በግፈኛ አገዛዝ እያለቀሰ የሚኖርን ገበሬ በሚያስለቅሰው ዘረኛ ሥርዓት ተደስቶና ደልቶት እንደሚኖር በሚያስገርም አነጋገር ሰይጣናዊ ስብከትን በመገናኛ ብዙኃን መልቀቅ ከይቅርታ በላይ ነው፡፡ ብሶቱን ችሎ፣ የሚደርስበትን ግፍና መከራ ተቋቁሞ በሞትና በሕይወት እየተንጠራወዘ በሚኖር ሕዝብ ላይ ይህን የመሰለ ቀልድና ድራማ እየሠሩ መሣለቅ ለዘር የሚተርፍ መራራ ቅጣት ሊያስከትል እንደሚችል በረከትም ሆነ ግብረ አበሮቹ መረዳት አለባቸው፡፡ ይህ መሪር ቀልዳቸው ዛሬና ለነሱ ምንም ላይመስል ይችላል፡፡ ይሁንና እያንዳንዷ የምናደርጋት መጥፎ ነገር ሁሉ ትልቅ ዋጋ ሳታስከፍል እንዲሁ የምትቀር እንዳልሆነች ቀልደኞቹና በኢቲቪ የሚገኙ ሆዳም ወናፎች ሁሉ ሊገነዘቡት ይገባል፡፡ ዛሬ ገበሬውም ሆነ ከተሜው አንደበቱ ተለጉሟል፤ አይናገርም፤ ሊናገርም አይፈልግም፡፡ ሰሚ ስለሌለውና ፈጣሪው ፊቱን እንዳዞረበት ስለተረዳ ሁሉም በዝምታ ተቀምጧል፡፡ ይህ ማለት ግን ዘመን አይለወጥም፣ ዝም ያለም ሁሉ ደንቆሮና አላዋቂ ነው ማለት አይደለም፡፡ ወያኔ እንዳልነበር ሁሉ የማይኖርበት ጊዜ ሲመጣ ሊከሰት የሚችለውን ትዕይንት አለማየት ነው፡፡ ያኔ እንደዛሬው እዩኝ እዩኝ እንደተባለ ሁሉ ደብቁኝ ደብቁኝ የሚባልበት ጊዜ መድረኩን ይረከባል፡፡ ጥጋብ ደግሞ ወደራብ መንዳቱ ያለና የነበረ ነው፡፡ የጠገበ የሚራብ የማይመስለው የመሆኑ መጥፎ አጋጣሚ ግን አሳዛኝ የታሪክ ግጥምጥሞሽ እንደሆነ እስካሁን አለ - ሲገርም፡፡ አንዱ ከአንዱ ገመና ትምህርት ቢገበይ፣ የሚነሣው ከሚወድቀው ቢማር ግና የችግሮቻችን መንስኤዎች እንደጤዛ በረገፉ፣ እንደጉምም በበነኑ ነበር፡፡ ይህ አለመታደል እስከመቼ እንደሕግ ሆኖ እንደሚበጠብጠን አላውቅም፤ እስኪ የመጨረሻችን ያድርግልን፡፡

በማጠቃለያዬ ማሳሰብ የምፈልገው ነገር አለኝ፡፡ በረከትም ሆንክ ሌላ ጊዜ ሰጠኝ የምትል ባለሥልጣን ሁሉ ካለፈው ታሪክ ተማር፡፡ የሚያሳዝነኝ ነገር አፄዎቹ ከቀደሙት አፄዎች መማር ሳይፈልጉ ቀሩ፤ ቀሩናም ሕዝብን ሲንቁ ሲንቁ ቆይተው በናቁት ሕዝብ እርግማንና አመፅ ምክንያት እንዳልሆኑ ሆኑ - ዘር እንኳን አልወጣላቸውም፡፡ ደርግም ፈጣሪን ሣይቀር ከድቶና አስከድቶ ራሱን የፈጣሪን ያህል በመቁጠር ሕዝብን ሲንቅና ሲያዋርድ ቆይቶ በናቀውና ባዋረደው ሕዝብ እርግማንና ሁለንተናዊ የእምቢታ አመፅ ሰበብ እንደባቢሎን አይሆኑ ሆኖ ተንኮታኮተ - ስንትና ስንት ዘመናዊ ትጥቅ እያለው አንዱም አላዳነውም፤ ይንቃቸው በነበሩ መናኛ የጫካ ወሮበሎች በቀላሉ ተገፍትሮ ወደቀ፡- መጽሐፉ ‹ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም› እንደሚል መዘንጋት አይገባም፡፡ እነዚህኞቹ ፀረ-ኢትዮጵያ ጉጂሌዎችም አይነጋ መስሏቸው የኢትዮጵያ ታሪክ መዝገብና ሕዝቡ ሊሸከሙት ያልተቻላቸው ግፍና በደል በሀገርና በሕዝብ ሠሩ፤ ዋናዎቹ የአገዛዙ ቁንጮዎች በሣምንታት ልዩነት ወደማይቀሩበት የሲዖል ሥፍራቸው ተጓዙ፤ ቀሪዎቹም በመኖርና ባለመኖር አጣብቂኝ ውስጥ ተሰንቅረው ያደርጉትን በማጣት ፈጣሪ ሩህያቸውን ጨርሶ እስኪወስዳት እየተንጠራወዙ ይገኛሉ - ይህን እውነት ማስተሃቀር ፈጽሞውን የሚቻል አይደለም፡፡ ለውስጥ አዋቂዎች ወያኔዎች በሕይወት እንደሌሉ ከገባን ቆይተናል፡፡ በሕይወት ያሉ እንዲመስሉ የሆነው ምናልባት ለበጎ ነው፡፡ እንጂ እንደእውነቱ ወያኔ አከርካሪው የተመታው ዋናውን የሥርዓቱን መሃንዲስ መለስ ዜናዊን ፈጣሪ ባልተጠበቀ ወቅት ገና በ‹ማለዳ ዕድሜ›ው ሲጠራው ነው፡፡ ልብ ከተገኘ "ሁሉም ከእያንዳንዱ፣ እያንዳንዱም ከሁሉም እንዲማር ጊዜ ለመስጠት ተብሎ ነው የወያኔ የማይቀር ኅልፈት አዝጋሚ እንዲሆን የተደረገው" ብሎ ማሰብም ይቻላል - ምንም ነገር ማሰብ በማንም አልተከለከለምና (ወያኔዎች ግን ይህንንም ተፈጥሯዊ መብት ሊነፍጉን ይቃጣቸዋል፤ ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖርክ ወያኔን ስለመጣል ወይም በሀገሪቷና በሕዝቡ ላይ የጣሉትን ግፈኛ የአገዛዝ ቀምበር ስለመቃወም "ማሰብ"ም አትችልም - ማሰብህ በዐይነ ውኃህ የፊት-ንባብ ከተደረሰበት በአሸባሪነት ተጠርንፈህ ዘብጥያ ትወርዳለህ)፡፡ ማሰብ በቻልንበት ሃሳብ ውስጥ በጊዜ ሰጪነት የምንጠረጥረውን አካል ደግሞ ለሁላችንም እኩል በሚገባን ቋንቋ አቶ ታሪክ ልንለው እንችላለን፡፡ ታሪክ የሚያዳላ ይመስለናል እንጂ ለማንምና ለምንም በጭራሽ አያዳላም - የራሱ የጊዜ ቀመር እንዳለው ግን ማጤን ተገቢ ነው (እርግጥ ነው - ‹መብሰሉ ለማይቀረው ጭንቅላት እንጨት ይፈጃል› እንደሚባለው አንድ ታሪካዊ ኹነት ተከናውኖ ቀጣዩ ሌላ ኹነት እስኪከናወን የሚኖረው የጊዜ እርዝማኔ በትግስታችንና በሃይማኖታችን ጭምር አሉታዊ ጥላውን ማጥላቱ የማናልፈው የዘመን ቅጣት ይመስላል፤ ማን ነበረች - አዎ፣ ሜሪ አርምዴ - "ፍቅር ያዘኝ ብለሽ አትበይ ደንበር ገተር፤ እኛም አንድ ሰሞን እንደሱ አ'ርጎን ነበር፤› ያለችውን የዘፈን ግጥም አለመዘንጋት የአጽናኝነት ጠቀሜታ አለውና እናስታውሰው፡፡) ዕድሜ ይስጠን ሁሉን እናያለን፡፡ ሌላ ዘፋኝም "እናያለን ገና" ብሏል፡፡ ይህንኑ ዘፈን ልጋብዛችሁና እንለያይ፡፡ ጣሊያኖች ሲለያዩ "አሪቬዴርቺ" ይላሉ - በ"ሰላም ያገናኘን" ለማለት፡፡

ሰበር መርዶ!

ይህን ጦማር ጽፌ የጨረስኩት ሌሊት ነው፡፡ ጧት ወደሥራ ልሄድ ስነሳ እንደወትሮው ሁሉ ቤቴ አጠገብ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቻቸውን ወደዬክፍላቸውን ከማስገባታቸው በፊት ሰንደቁ አጠገብ አሠልፈው ብሔራዊ መዝሙር በቴፕ ከፍተው ሲያጮኹ ሰማሁ፡፡ ይሄኔ ኮምፒውተሬን ከፍቼ ይህችን ሃሳብ በሰበር መርዶነት ለመሰንቀር ወደድኩ፡፡ የሀገር ሞት ከዚህ በላይ የለም፡፡ በጥንት ጊዜ ብሔራዊ መዝሙር ተማሪው ነበር በስሜት ተውጦ በመዘመር ወደክፍሉ የሚገባው፡፡ አሁን ዕድሜ ለወያኔ አዲሱ መዝሙር ሊያውም በመሣሪያ ብቻ የተቀነባበረው በቴፕ ይዘፈንና ወደክፍል ይገባል፡፡ ዛሬ ዛሬ የኢትዮጵያን ብሔራዊ መዝሙርና ባንዴራ የሚያውቅ ትውልድ እየጠፋ ነው፡፡ ራሱ መለስ ዜናዊ (በሕይወት ኖሮ) ይህን መዝሙር ውጣው ቢባል የሚችለው አይመስለኝም፡፡ ሌሎቹ የወያኔ ባለሥልጣናት ቢጠየቁም የሚያውቁት ስለመሆናቸው እርግጠኛ መሆን አይቻልም - ብቸኛ ዘመዳቸው ሆዳቸው በመሆኑ ስለሀገር ምንነት የሚያውቁት ነገር የለም ማለት ይቻላል፡፡ የሚሰቀለው ባንዴራ ደግሞ የተቀዳደደ፣ የነተበ፣ ቀለሙን የለወጠ፣ ከተሰቀለ የማይወርድና ተበጣጥሶ እስኪያልቅ 24 ሰዓት የሚውለበለብ የማን ሀገር ባንዴራ መሆኑም የማይታወቅ ነው፤ የጥንቱን የባንዴራ አሰቃቀልና አወራረድ ሥርዓት የሚያስታውስ ዜጋ የአሁኑን ሲያይ ያለቅሳል፡፡ ከአዲስ አበባ ወጣ በሚል ቦታ ደግሞ የኦሮሚያ ባንዴራና የኦሮሚያ ብሔራዊ መዝሙር በትምህርት ቤቶች እንደዚሁ በቴፕ ሲዘመር ወይም ልጆች በግዴታ አጥንተው እንዲዘምሩት ሲደረግ ታያላችሁ፡፡ ይህችን የነፃነት ምኩራብ የሆነች የታሪክ አምባ ሀገራችንን እንዲህ ባለቤት ያሳጧት የሰይጣን ልጆች ዋጋቸውን ሳያገኙ ከቀሩ በርግጥም ኢትዮጵያ ፈጣሪ የላትም፡፡ አላስችል ብሎኝ አሁን በእግረ መንገድ ትንሽ ለመናገር ፈለግሁ እንጂ ይህ ጉዳይ ብዙ የሚያናግር ነው - የጋራ የሚባለል አንዳችም ነገር እንዳይኖረን ከፍተኛ የጥፋት ሥራዎች በመሠራታቸው አሁንና ለጊዜው ጠፍተናል፤ አለን እንላለን እንጂ በርግጥም በወኔያዎች ደባና ሤራ የአብሮነት ኅልውናችን አደጋ ላይ ወድቋል - ብዙ የትስስር ገመዶች ተበጣጥሰዋል፡- የጋራ ቋንቋ፣ የጋራ መሪ(ዎች)፣ የጋራ የመከላከያ ጦር፣ የጋራ የፖሊስ ሠራዊት፣ የጋራ ድንበር፣ የጋራ ባህል፣ የጋራ ትውፊት፣ የጋራ ሥነቃልና ሥነ ጽሑፍ፣ የጋራ ቤተ መንግሥት፣ የጋራ መንግሥታዊ መዋቅር፣ የጋራ... የጋራ... የጋራ... የምንለው ነገር እንዳይኖረን ተደርገን አንዳችን አንዳችንን የጎሪጥ እንድናይና እንድንፈራራ ተደርገናል፡፡ ሌላው ሁሉ ቀርቶ የጋራ ስብዕና ወይም የሰውነት ደረጃ እንኳን የለንም፤ አንዱ ከሌላው የበለጠ ሰው ነው - ሌላውም ከአንዱ ያነሰ ሰው ነው፡፡ አንዱ የሰው ዘር ከሌላው በተለዬ ምርጥ ነው - ሌላው ደግሞ ውዳቂና ቢገድሉት የበቃ ነፍሱ ከእንስሳት ነፍስም ሳይቀር ያነሰ ዋጋ ያለው ነው - ሩቅ ተመልካቹ ጆርጅ ኦርዌል ጨርሶታል - "All animals are equal, but some are more equal than the others."፡፡ በዚህ መልክ በፈረጁን ሰዎች ነው እንግዲህ አጥንታችን ድረስ ዘልቆ በሚጠዘጥዝ መሪር ፈረያናዊ አገዛዝ እየተቀጠቀጥን የምንገኘው፡፡

ያን ደገኛ ኢትዮጵያዊ የአንድነት መንፈስ ለማምጣት እነቴዲ አፍሮን የመሰሉ የቁርጥ ቀን ልጆች ብቻ ሣይሆኑ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ሰመጉ ቁጫ ወረዳ ዉስጥ ከ400 በላይ ሰዎች በግፍ ታስረዋል ሲል ኡኡታዉን አሰማ

ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚገኘዉና የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ እየተባለ የሚጠራው አንጋፋው የሰብአዊ መብቶች ተከራካሪ ድርጅት ቁጫ ወረዳ ዉስጥ ከ400 በላይ ሰዎች አግባብ ካለዉ የህግ ሂደት ዉጭ መታሰራቸዉ እንዳሳሰበዉ ገለጸ። ድርጅቱ ሰሞኑን አዲስ አበባ ዉስጥ ባወጣው መግለጫ በሰላም በር ፖሊስ ጣቢያ 198 ሰዎች ፣በአርባ ምንጭ ማረሚያ ቤት ደግሞ 212 ሰዎች ” መታሰራቸውንና ከዚህ አስር፤ በደልና እንግልት ለማምለጥ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የወረዳዉ ነዋሪዎች ወደ አጎራባች ወረዳዎች መሰደዳቸውን” ገልጿል። መኖሪያ ቤቶች ያለ ፍረድ ቤት ትዕዛዝ መበርበራቸውን፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሰራተኞች ጥያቄውን ደግፋችኋል በሚል ከስራ መፈናቀላቸውን፣ አራት ግለሰቦች ለከባድ የአካል ጉዳት መዳረጋቸውንና የአንድ ሰው ህይወትም ማለፉን ሰመጉ ገልጿል።

“ህዳር 14፣ 2006 ዓ.ም ከቀኑ 7 ሰአት ቶኮ ደንቢያ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አካባቢ ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦች ትምህርት ቤቱ ሊዘረፍ ነው ብለው ባመለከቱት መሰረት በተጠራ ስብሰባ ላይ የ8 ቀበሌዎች ህዝብና የአካባቢው ባለስልጣናት ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ ቀጥረው በመመለስ ላይ ሳሉ የቁጫን ህዝብ ዘፈን እየዘፈኑ ሲሄዱ ከነበሩት ተሰብሳቢዎች ውስጥ ዝም እንዲሉ ታዘው ባለመታዘዛቸው መዝፈን የቀጠሉት አቶ ዛራ ዛላ የወረዳው ፖሊስ አዛዥ ዋና ኢንስፔክተርና የወረዳው አስተዳዳሪ የስጋት ስንታ በተገኙበት የወረዳው አስተዳደር ሹፌር አቶ ወንድወሰን ሳልሌ በክላሽ ጥይት ተኩሶ ገድሏቸዋል” በማለት ነዋሪዎች ለሰመጉ አቤቱታ ማቅረባቸውን መግለጫው ጠቅሷል። “ቤተሰቡ አስከሬኑን እንዲቀብር በባለስልጣናት ቢጠየቅም ሳናስመረምር አንቀብርም በማለታቸውና ባለስልጣናቱ ለማስመርመር ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ከቤተሰቡ እውቅና ውጪ በማዘጋጃ ቤት የመቃብር ቦታ ህዳር 17 ቀን 2006 ዓ.ም ከምሽቱ 1 ሰአት እንደተቀበረ መግለጫው ጠቁሟል።

ሟቹ የ35 አመት ጎልማሳ፣ ባለትዳርና የሶስት ልጆች አባት እንደነበሩ ታውቋል። ተጠርጣሪዎቹም ይህ ሪፖርት ሪፖርቱ እስከተጠናከረበት ጊዜ ድረስ ለፍርድ አልቀረቡም። በተመሳሳይ መንገድ በካስኬ ገንዜ ቀበሌ ነዋሪ የሆነው አቶ አፈወረቅ አበራ በተመሳሳይ ቀን ከአቶ ዛራ ዛላ ጋር አብሮ የነበረ ሲሆን የቁጫ ወረዳ አስተዳደር ሹፌር የሆነው ወንደወሰን ሳልሌ በክላሽ ጥይት በጀርባው ላይ እንደመታውና በሰላም በር ጤና ጣቢያ በመታከም ላይ እንደሚገኝ የቁጫ ህዝብን ዋቢ በማድረግ የሰመጉ ልዩ መግለጫ ያብራራል።

በጌሬራ ቀበሌ ነዋሪ የሆነው አቶ ደባራ ደርዛ በ6/03/2006 ዓ.ም ከቀኑ 11:30 ላይ ቅዳሜ ገበያ ለመሄድ ተነስቶ ሞጎላ ቀበሌ ሲደርስ የወረዳው የፀጥታ ሃላፊ የነበረው አቶ አያኖ መሰኔ እና የወረዳው ፖሊስ አባል በየነ ባንጃ እንደተተኮሰባቸውና በሁለት ጥይቶች ግራ እግራቸው ላይ ተመተው ከ7/04/2006 ዓ.ም ጀምሮ በሶዶ ክርስቲያን ሆስፒታል በመታከም ላይ እንደሚገኙ ሰመጉ ገልጿል። የ75 አመቱ አዛውንት አቶ ጨለቦ ጨማ ህዝቡን ወክለህ አዲስ አበባ ሄደህል ተብለው ከ11/3/2006 ዓ.ም ጀምሮ ሰላም በር ፖሊስ ጣቢያ እንደታሰሩና እንደተደበደቡ ከ180 ሰዎች በላይ አብረዋቸው እንደታሰሩና ዋስ ጠርተው በህክምና ላይ እንደሚገኙ ህክምናውን ሲጨርሱም ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንደሚመለሱ በሆስፒታሉ ሆነው ቃላቸውን መስጠታቸውን መግለጫው ይጠቅሳል።

መግለጫው 46 የመንግስት ሰራተኞች ከስራ መባረራቸውን የስም ዝርዝራቸውን በመጥቀስ ይፋ አድርጓል። ሰመጉ በመጨረሻም ” መንግስት ይህንን መሰረታዊ የማንነት ጥያቄ በሕግ አግባብ በአፋጣኝ መልስ እንዲሰጥበት፣ ለተፈፀሙት ወንጀሎች ማለትም ለግድያ፣ ለአካል መጉደል፣ ድብደባ፣ ሕገ-ወጥ የቤት ብርብራ፣ ህገ-ወጥ እስርና፣ ለስራ መሰናበት ምክንያት የሆኑትን ግለሰቦች በህግ አግባብ እንዲጠየቁ እንዲያደርግ፣ ግድያ፣ የአካል ጉድለትና ከስራ መሠናበት ለደረሰባቸው ግለሰቦችና ቤተሰቦች ተገቢውን ካሳ እንዲያሰጥ እንዲሁም በየአጎራባች አካባቢዎች ለተሰደዱት የተረጋጋ የኑሮ ሁኔታ ዋስትና በመስጠት ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው ተመልሰው ሰላማዊ ኑሮአቸውን የሚመሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንዳለበት በአፅንኦት ጠይቋል።

## ስድስት ሚሊዮን ኢትዮጵያዉያን የምግብ ዋስትና እንደሌለቸዉ ታወቀ

ወያኔ የገበሬ ሚሊዮነሮች አፈራን እያለ በሚናገርባትና የግብርናዉ ዘርፍ እጅግ በጣም ፈጣን ዕድገት እያሳየ ነዉ ተብሎ በሚዘፈንባት ኢትዮጵያ ዉስጥ ከ6 ሚሊዮን በላይ ህዝብ (አብዛኛዉገበሬ) ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ስለገጠመዉ ይህ ችግር ላይ የወደቀ ገበሬና ቤተሰቦቹ በሴፍትኔት መታቀፋቸውን የግብርና ሚኒስትር አስታወቀ፡፡ እንደ አዉሮፓዉያኖቹ ዘመን አቆጣጠር በ2013 ለሁለተኛው አጋማሽ ማለትም ከሀምሌ እስከ ታህሳስ የአስቸኳዋይ ጊዜ እርዳታ ለሚያስፈልገው 2 ነጥብ 7 ሚሊየን ሕዝብ የሚውል 162 ሺህ176 ሜትሪክ ቶን ምግብ ውስጥ ማሙዋላት የተቻለው 69 በመቶ ያህሉን ብቻ በመሆኑ ብዙ ህዝብ ለአደጋ ተጋልጦ ይገኛል ሲል የአገሪቱ ግብርና ሚኒስትሩ ተፈራ ደርበው ለፓርላማዉ አስረድቷል። የግብርና ሚኒስትሩ ለዚሁ ወያኔ ያቀረበለትን ሁሉ መስማትና ማጽደቅ እንጂ መፍትሄ መፈለግ ለማያዉቀዉ ፓርላማ ባቀረቡት የስድስት ወራት ስራ አፈጻጸም ሪፖርት በድርቅ ችግር ውስጥ ላለው ወገን የሚያስፈልገው የምግብ መጠን እና አቅርቦት መካከል ከፍተኛ ልዩነት መኖሩን በይፋ ተናግረዋል፡፡ በዚህ ምክንያት የሴፍቲኔት ፕሮግራም ባለባቸው ወረዳዎች የተያዘው የመጠባበቂ በጀት በመጠቀም ቀሪው አቅርቦት እንዲሟላ ተደርጎአል ብለዋል፡፡ በተጨማሪም ባለፉት ስድስት ወራት ከግጭት እና ከጎርፍ ጋር በተያያዙ ችግሮች ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው 1 ነጥብ 5ሚሊየን ሕዝብ ምግብ ነክና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታ ለመስጠት ታስቦ ለ245 ሺህ 385 ሕዝብ ብቻ መሰጠቱን ተናግረዋል።

በበጀት ኣመቱ 2 ነጥብ 1 ሚሊየን ህዝብ ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸውን ወገኖች በልማታዊ ሴፍትኔት ለማሳተፍ ታቅዶ 6,ሚሊዮን 3 ሺ 551 ቤተሰቦች በፕሮግራሙ ማሳተፍ መቻሉን አስረድተዋል። ይህ ሊሆን የቻለው ከአፋርና ሶማሌ ክልሎች 32 አዳዲስ ወረዳዎች በፕሮግራሙ በመካተታቸው ነው ብለዋል። ከድርቁ ጋር በተያያዘ ለቤተሰብ ጥሪት ግንባታ በየወረዳው የሚሰጠው ብድር በወቅቱ ተመልሶ ለቀጣይ ብድር አገልግሎት ማዋል ያለመቻል፣ተጨማሪ ብድር በሚፈለገው መጠን ያለማቅረብ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች በተደጋጋሚ የሚከሰተው ድርቅ ተጠቃሚዎች እንዳያንሰራሩ ማድረጉ፣ በአመራሩም ሆነ በባለሙያው በቂ ድጋፍና ክትትል ያለማድረግ የሚሉትን በችግርነታቸው አንስተውታል።

## ወያኔ ለሱዳን አሳልፎ የሚሰጠው የአገራችን መሬት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ሲያሰሙበት የቆዩ ቢሆንም የፋሽስቱ ወያኔ ቁነጮዎች ግን ሲያስተባብሉ መቆየታቸው ያታወሳል። ሆኖም ግን በቅርቡ ከራሷ ከሱዳን ከፍተኛ ባለስልጣናት ተገኘ የተባለው የጉዳዩን እውነተኛነት የሚያረጋግጠው ዜና ከተሰማ በኋላ በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን በአንድነት አስተባብሮ ለተቃውሞ እንዳቆመ ታውቋል። በጉዳዩ ላይ ትዝብታቸውን የሚናገሩ ወገኖች እንደሚሉት ደግሞ ”ያለምንም የሕዝብ ውክልና የአገዛዝ ወንበርን በጉልበቱ ተቆጣጥሮ ያለው ፋሽስት ወያኔ በአገዛዝ ዘመኑ ከሕዝብ ይሁንታ ውጭ በሀገርና በሕዝብ ላይ የፈጸማቸው ወንጀሎች ወደ ፊት ሕዝባዊ መንግስት ሲኖርን ጥያቄ የሚነሳባቸው መሆኑን በማስገንዘብ በፋሽስት ወያኔ ያላግባብ ለሌላ ሀገር እየተላለፈ ያለው መሬታችንም ወደ ፊት በህጋዊ መንገድ ይመለሳል። ለዚህ ደግሞ እኛም እስካለን ክንዳችንን አናጥፍም ለወደፊቱም ታሪኩን ለልጆቻችን እናወርሳለን” ይላሉ።

## አንድ አለማቀፍ ተቋም ወያኔ የግንቦት 7 መሪዎችን በዉድ ዋጋ በተገዛ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ፕራይቬሲ ኢንተርናሽናል በደብዳቤው ገልጿል። የመሰለያ መሳሪያው የሰብአዊ መብቶችን በሚጥሱ 36 አገራት ላይ መሸጡን የገለጻው ፕራይቬሲ ኢንተርናሽናል፣ በተለይም በቬትናም፣ ማሌዚያና ኢትዮጵያ የፖለቲካ ተቀናቃኞችን ለመሰለያነት እየዋለ ነው ብሎአል። በኢትዮጵያ የግንቦት7 ከፍተኛ አመራር የሆኑት ዶ/ር ታደሰ ብሩ ኮምፒተራቸው ሲሰለል መቆየቱን የገለጸው ፕራይቬሲ ኢንተርናሽናል፣ በአንድ የብሃሬን የሰብአዊ መብት ተማጓች ኮምፒዩተር ላይም ተመሳሳይ የስለላ ሶፍት ዌር መገኘቱን ገልጿል።

ዶ/ር ታደሰ ብሩ ለፕራይቪሴ ኢንተርናሽናል ጠበቃ የምስክርነት ቃላቸውን መስጠታቸውን ተናግረዋል። ፕራይቪሲ ኢንተርናሽናል የስለላ ቫይረሱን የሸጠውን ጋማ ኢንተርናሽናልን የተባለውን ድርጅት ወደ ፍርድ ቤት ለመውሰድ ማቀዱን ዶ/ር ታደሰ ገልጸዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ስሞኑን የተለቀቀው የዘንድሮው የሂውማን ራይትስ ወች ሪፖርት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በጉልበት ካልሆነ በቀር በማንኛውም ሰላማዊ መንገድ ስልጣን ለማስረከብ ዝግጁ እንዳልሆነ በተደጋጋሚ በዓለም ፊት ያስመሰከረው ፋሽስት ወያኔ ከዚህ በፊት ሂውማን ራይትስ ወችን ጨምሮ በሌሎችም ዓለማቀፍ ተቋማት ሪፖርት የተሰነዘረበትን ትችት ሁሉ ውሸት በማለት ሲያስተባብል እንደቆየ አይዘነጋም።

እንደራደር ወይም እንወያይ በሚል የሞኝ ፈሊጥ የነጻነት ታጋዮችን ግዜ ለመግደልና አላማቸዉን ለማሳት ሆን ብሎ መንቀሳቀስ የጀመረዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ናይሮቢ ኬንያ ዉስጥ በኬንያ መንግስት አማላጅነት ለድርድር የተጋበዙትን ሁለት የኦብነግ መሪዎች አፍኖ አዲስ አበባ መዉሰዱን የኦጋዴን ነጻነት ግንባር ገለጸ። በሳምንቱ አጋማሽ ላይ ግንባሩ ለኢሳት ሬድዮኛ ቴሌቪዥን በላከው መረጃ ከመንግስት ጋር ለመደራደር ኬንያ የሚገኙት የኦነግ ከፍተኛ አመራር አባላት ሱሉብ አህመድና አሊ ሁሴን በኢትዮጵያ የጸጥታ ሃይሎች ታፍነው ወደ አልታወቀ ቦታ ተወስደዋል። መሪዎቹ የታፈኑት ናይሮቢ ውስጥ ሲሆን፣ ከመንግስት ጋር ለሚደረገው ሶስተኛ ዙር ውይይት ዝግጅት እያደረጉ ነበር።

ግንባሩ በመግለጫው ከዚህ ቀደምም የመንግስት የጸጥታ ሃይሎች የኦብነግ መሪዎችን ሲገድሉና ሲያፍኑ ነበር ብሎአል። በፈረንጆች አቆጣጠር በ1998 5 የኦብነግ አመራሮች ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ድርድር ሲያካሂዱ ከቆዩ በሁዋላ 3ቱ ሲገደሉ 2ቱ ደግሞ ተጠልፈው ተወስደዋል። ከሁለት አመት በፊት ደግሞ የግንባሩ ከፍተኛ አመራር ናይሮቢ ውስጥ ተገድሏል። ግድያው ከመንግስት ጋር የሚደረገውን ቀጣይ ድርድር እንደሚያበላሸው የገለጸው ኦብነግ፣ ይህ የፈሪዎች ድርጊት የኦጋዴን ህዝብ ለነጻነቱ ይበልጥ መቆም እንዳለበት የሚያስገነዝብን ነው ሲል አክሏል። ግንባሩ ሁለቱ ሃይሎች እንዲደራደሩ ሁኔታዎችን ያመቻቸው የኬንያ መንግስት ጣልቃ ገብቶ ሰዎቹ እንዲለቀቁ እንዲያደርግ ጠይቋል። የኬንያ መንግስት ሀላፊነት ወስዶና በአማላጅነት ለዉይይት የጋበዛቸዉ ሦስተኛ ወገን አባላት አማልደኝ ብሎ በጠየቀዉ መንግስት የጸጥታ አባላት ተጠልፈዉ ሲወሰዱ ዝም ብሎ መመልከቱ በአፈናዉ ላይ እጁ ሊኖርበት የችላል በለዉ እንደሚያምኑ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ተናግረዋል። አሁንም ቢሆን ኬንያ ተዓማኒነቷን ለማረጋገጥና አለም አቀፍ ህጎች ግዴታዋን ለመወጣት የታፈኑትን የኦብነግ መሪዎች በተለከተ የኢትዮጵያን መንግስት ባለስልጣኖች ማብራሪያ መጠየቅና የሁለቱን ሰዎች ደህንነት ማጋገጥ እንደሚኖርባት ብዙዎች ይስማማሉ።

## ወያኔ/ኢህአዴግ የልማት ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

መካከለኛ ገቢ የሚባለው ከገቢ አንጻር ሲሰላ ዝቀተኛው 1000 ዶላር ከፍተኛው ደግሞ 5 ሺ ዶላር መሆኑን የጠቀሰዉ በረከት ባለፉት 10 አመታት የጀመርነውን እድገት ከቀጠልን በሚቀጥሉት 10 አመታት የመካከለኛው ገቢ ዝቀተኛ ጣራ ከሆነው 1000 ዶላር የነፍስ ወከፍ ገቢ ደረጃ ላይ እንደርሳለን በማለት አፋቸዉን ከፍተዉ መስማት ብቻ እንጂ እንዴት ወይም በምን ስሌት ብለዉ መጠየቅ የማይችሉትን የፓርቲዉን ካድሬዎች አስደምሟል። ጉደኛዉ በረከት በዚህ ብቻ አላቆመም፤ የመካከለኛ ገቢ ከፍተኛ ጣራ ከሆነው 5 ሺ ዶላር የነፍስ ወከፍ ገቢ ለመድረስ እንደገና ተጨማሪ 15 ወይም 20 አመታት ይወስድብናል ብለዋል። በበረከትና መሰሎቹ እዉራን የሚመራዉ የወያኔ አገዛዝ ካለመታከት ሃያ አመት ሙሉ ሳያሰልስ ካሳይን ነገሮች አንዱ ለቍጥር፤ በመረጃ ለተደገፈ ገለጻና ለእስታቲስቲክስ በፍጹም ግድ የሌለዉ መሆኑን ነዉ።

የከፍተኛው ገቢ የመጨረሻው ደረጃ ለሆነው የ10 ሺ ዶላር የነፍስ ወከፍ ገቢ ደረጃ ለመድረስ ሌላ ከ15-20 ተጨማሪ አመታት እንደሚያስፈልግ አቶ በረከት አክለዋል። ይህንን ጊዜ ለማሳጠር ብንፈልግ ልናሳጥረው አንችልም የሚሉት አቶ በረከት፣ እድገቱ አንዳንዴም ልክ ቱኒዚያ፣ ታይላንዳና ማሌዢያ እንደተቋረጠባቸው ሊቋረጥ ይችላል ብለዋል። ይህን እድገት ለማስቀጠል ፈተናዎች አሉ ያሉት አቶ በረከት፣ አንደኛው ፈተና እድገቱን ህብረተሰቡ ሳይሰለች ማስቀጠል ይችላል ወይ የሚለው ነው ሰሉ ተናግረዋል። "ነባሩ አመራር በእድሜ፣ በጤናና በመድከም ከሃላፊነት የሚወጣ በመሆኑ አዲሱ ትውልድ በተመሳሳይ ትኩረትና ፍጥነት እድገቱን ይዞት ሊሄድ ይችላል ወይ?' የሚለው ጥያቄ ያልተመለሰና መመለስ ያለበት ነው ሲሉ ኢህአዴግ ያጋጠመውን ፈተና ገልጸዋል። ኢሳት የድምጽ መልእክቶችን በመላክ የሚተባበሩንን ከፍተኛ የኢህአዴግ አመራሮች ለማመስገን ይወዳል።

## የወያኔ ነፍስ በበረከት ስምዖን በኩል ስትቃኝ

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

ሁላችንም የየበኩላችንን ጥረት ማድረግ ይኖርብናል - ለራሳችንና ለልጆቻችን ስንል። ከራስ ወዳድነትና ከአህያይቷ የ‹እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል› ያረጀ ያፈጀ አስተሳሰብም ባፋጣኝ እንውጣ። አርቀን መመልከትን ባህላችን እናድርግ። ጎርፉ ሳይደርስብን ራሳችንን በጎሊና ጸጸት አጥበን ለመጪው መልካም ኢትዮጵያዊ ዘመን ዝግጁ ሆነን ለመጠበቅ እንሞክር። በየድረ ገጹ የሚታዬው ዘረኝነት ላይ የተመሠረተ ወያኔያዊ የዱባ ጥጋብ መሰል ቡራከረዩና ወንዝ የማያሻግር ከፋፋይ ፕሮፓጋንዳ ዘመኑን እያገባደደ በመሆኑ የአንዲት እናት ልጆች ነንና እንሶብር። ወያኔ የጋተንን ብርብራና መቅመቅ ማርከሻ እንፈልግለት፤ "ስሜት-ወለድ" ማስጠንቀቂያየን እዚህም ላይ ልድገመው - "እዩዩኝ ያለ ደብቁኝ ደብቁኝ ይላል"። ====//====

## ሐቁ ተሰደደ!

ትናንትሽን ከአድማስ ማዶ
ባዕድ ሀገር ማንስ ወዶ

እኔና እናንተ እኮ ከአመታት በፊት
በታሪክ በሃይማኖት በባህል በትውፊት

በጋሻና በጦር ጀብደኛ ባለሀገር
የአንድ አያቶች ዘር የአንድ አፈር ሰፈር

ግና ዛሬን ይኸው ይከፋፍሉናል
እራስን ከፍ አርገው ትንሾች ይሉናል

በስልጣን ከፍ ከፍ
በሃብትም ከፍ ከፍ
የወደቁ ለታ ማንነት እንዳይተርፍ

ትንሹ ነብዩ በጥይት ተገድሎ ያላንዳች ጥፋቱ
ያለ ፍትህ ታስሮ ስንቱ ወገኔ ሞቶ ወጣት አዛውንቱ
ይሄ ሁሉ ጥፋት ፍትህ አልባነቱ
የየኔ ሰው ገብሬ በእሳት መሞቱ

የሐረሩን እንቡጥ ተሰፋችን የነገው
ቀጥቅጥጠው ገደሉት ባልዋለበት ውለው

እስክንድር ፤ አንዱአለም፤ ናትናኤል፤ ርዕዮት አለሙ
ያለ ምንም በደል በግፍ የታሰረው ክርስቲያን ሙስሊሙ

ፍትህ ቢጎድልበት ተገፍትሮ የወጣው
በሳውዲ አረቢያ ደሙ ለፈሰሰው
የወገኔን እንባ ወገኑ አበሰው
ይብላኝ ለወያኔ ቀኑ ለደረሰው

ማዳመጥ አይሻ ተቃዋሚ አፍርሶ
እኔ ብቻ አዋቂ ጭራሽ ተኮፍሶ

በአኬልዳማ ሽብር ህዝብ እያሳደደ
ውሸት ተደላድሎ ሐቁ ተሰደደ።

ምንድን ነው ነፃነት?
ባርነት ምን ሲባል ብለው የታገሉት
ለነፃነት ብለው ህዝብ ላይ ጉብ ያሉት
አዋቂ ነን ብለው ታሪክ ያጎደፉት

ከዚህ መልስ ኦሮሞ
ከዚያ መልስ ጋሞ
ከዚህ መልስ ሲዳማ
ከዚያ መልስ ኩናማ

አንድነት በትነው
ህጉን አፈራርሰው
ከፍፍልን ዘርተው

ይሄ ነው ነፃነት ስንቱ የሞተለት?
ይበቃል ከእንግዲህ ጨለማ አንፈልግም
ብትደበዝዝ እንጂ እውነት ጠፍታ አታውቅም። (2x)

ከሀና ሰመረ (ኖርዌይ)
hannasemere@yahoo.com